የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ
የህዝብ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
የሰው ኃብት ስምሪትና መረጃ ቡድን

City Government of Addis Ababa
Nifas Silk Lafto Sub-City
Office of Public Service and Human Resource Development, Human Resource Deployment and Info Team

ቁጥር፡-የሠ/ኃ/ስ/መ/ቡድን/ 939 /ሠ3 ቀን 3/13/2014ዓ.ም

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ለ ወረዳ 01 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 02 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 04 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 05 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 06 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 09 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 10 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 11 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
ለ ወረዳ 12 ጤና ጣቢያ የሰው ኃብት አስተዳደር ቡድን
አዲስ አበባ፣

ጉዳዩ፡ - የሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም ክፍያን ይመለከታል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ በቁጥር 57-ጠ11-17/32/245 በቀን 2/13/2014 ዓ.ም በተጻፈልን ደብዳቤ የሰራተኞች የቤት ኪራይ ድጎማ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች በገቢርገር በማጽደቅ የላከልን ሲሆን የተላከልንን ሰርኩላር ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እያሳውን ከሐምሌ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያው ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አመቤት ዘርጋው ዘውዴ
የሰው ሀብት ስምሪትና መረጃ
ቡድን መሪ

ክ/ከተማ አስተዳደር
ሕ/አ/ሰና የሰው ሀብት ልማት
ቢሮ

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT
PUBLIC SERVICE AND HUMAN
RESOURCE DEVELOPMENT BUREAU

ቁጥር 03-ማህ-17/32/245 ቀን 2-13-14
Ref. No. Date

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
- ለአራዳ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለለሚ ኩራ ክ/ከተማ ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት

አዲስ አበባ፣

ጉዳዩ፡ **የሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም ክፍያን ይመለከታል፣**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በቁጥር አአከ/ 17/02/8 በቀን 02/13/2014 ዓ.ም በተፃፈዉ ደብዳቤ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ ተዘጋጅቶ ለክቢኔ የቀረበዉ የመንግስት ሠራተኞች የቤት ኪራይ ድጎማ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች የከተማ አስተዳደሩ ክቢኔ ነሐሴ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደዉ 2ኛ ዓመት 3ኛ መደበኛ ስብሰባ በማዕደቱ ይኸዉ ታዉቆ ተግባራዊ እንዲደረግ በማለት አሳዉቆናል፡፡

በዚሁ መሠረት የተፈቀዱ የጥቅማ ጥቅም ዝርዝሮች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ በተላከላችሁ .....ገጽ ሰነድ መሠረት ከሐምሌ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያዉ ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
ለሰዉ ሀብት ልማትና አስተዳደር ዘርፍ
አዲስ አበባ

ሂኩማ ቢሪዲን መሃመድ
በምስክርነት ማዕረግ የፐብሊክ
ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት
ቢሮ ኃላፊ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፐብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ

የመንግስት ሰራተኞችን
ጥቅማ ጥቅም ለማስወሰን ለካቢኔ የቀረበ ሰነድ

ነሐሴ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

1. መግቢያ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከማዕከል እስከ ወረዳ በተዘረጋው መዋቅር 161,463 ቋሚ እና 4,800 ኮንትራት ሰራተኞች በተለያየ ስራ መደቦች ላይ የተሰጣቸውን ሀላፊነት ለመወጣት ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል። ሆኖም የመንግስት ሰራተኛው በተለያየ የክፍያ ስርዓት ውስጥ የቆየ ቢሆንም ይህን ችግር እንደ ሀገር ይፈታል ተብሎ የተጠበቀው የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ከደመወዝ አንፃር የተወሰነው ከሚጠበቀው በታች በመሆኑ አሁንም በመንግስት ሰራተኛው ከፍተኛ ቅሬታ ሆኖ ቀጥሏል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢትዮጵያ ዋና ከተማ እና ሜትሮፖሊታን ከተማ ከመሆኗ አንፃር በተለይም በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት መቋቋም ያልቻለው የመንግስት ሰራተኛ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ጫና እየፈጠረና የግል ህይወቱን ለመምራት በእስቸጋሪ ሁኔታ ላይ የደረሰ ሲሆን ለአብነት የመንግስት ሰራተኞች የወር ደመወዝ በወር ከብር 5,000.00 በታች የሚከፈላቸው ከአጠቃላይ ቁጥር ኢታይ 82,602 ወይም 51% እንደሆነ ከ2013 አመታዊ የሰው ሀብት መረጃ ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን የኑሮ ውድነት፤ የመኖሪያ ቤት ችግር፤ የህክምናና መድሀኒት ወጪ ከአቅም በላይ መሆን፤ ራስንና ቤተሰብን መመገብ አለመቻልና የመሳሰሉት ችግሮች ሰራተኛው የመንግስት ስራውን ተረጋግቶ እንዳይሰራ አድርጎታል። ስለሆነም ከላይ በተጠቀሱት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ለሰራተኞች ድጎማ ማድረግ ያስፈልጋል።

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የቤት ኪራይ ክፍያ፤ የትራንስፖርት ወጪ፤ የህክምና ወጪ እና በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የኑሮ ጫና መካሻ በማድረግ እና የከተማ አስተዳደሩን የመክፈል አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ለመንግስት ሰራተኞች ጥቅማ ጥቅም በማጥናት ይህን ሰነድ ለካቢኔ ወሳኔ አቅርቧል።

ጠቅላላ

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሰነድ ውስጥ፡-

2.1 "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፣

2.2 "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፣

2.3 ‹‹አዋጅ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ 56/2010 ማለት ነው::

2.4 ‹‹ቢሮ›› ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ማለት ነዉ::

2.5 ‹‹ሠራተኛ›› ማለት በከተማ አስተዳደሩ በመንግስት ሰራተኞች በአዋጅ 56/2010 በሚተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ውስጥ በቋሚነት እና በኮንትራት ተቀጥረው የሚያገለግሉ ሠራተኞች ማለት ነው::

2.6 «የጤና ተቋም» ማለት በከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ ስር የሚገኙ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎችን ማለት ነው::

2.7 «የጤና ባለሙያ» ማለት አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠና በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ውስጥ የተመደቡ ባለሙያዎች ማለት ነው::

2.8 **«ሙያዊ የሥራ ሀላፊነት አበል»** ማለት ከስራው ባህሪ አንፃር የስራው ክብደት፣ ውስብስብነትና የውሳኔ ሰጪነት ሚናው ከፍተኛ በመሆኑ ይህን ታሳቢ ያደረገ በሙያዉ እንዲያገለግል ሀላፊነት ለተሰጠዉ የሥራ መሪ የሚከፈል የክፍያ መጠን ማለት ነው::

2.9 **«የትራንስፖርት አበል»** ማለት አንድ በሙያዉ እንዲያገለግል ሀላፊነት የተሰጠዉ የስራ መሪ ባለበት ከፍተኛ ሀላፊነት ምክንያት ከመንግስት የስራ ሰዓት በላይ እያመሸ ስለሚሰራ፣

በዕረፍትና በበዓላት ቀናት ገቢው ስለማሰራ ይህንን ሰማሽህ ተብሎ ከወሩ ከየሰዓቱ የሚሰጥ አበል ማለት ነው።

2.10 «የሞባይል ስልክ ክፍያ» ማለት በስራው ዙሪያ ከተለያዩ አካላት ጋር ለማያገናኛቸው የስልክ መረጃ ልውውጥ ለሚያወጠው ወጪ የሚከፈል ክፍያ ማለት ነው።

2.11 «የአስተዳደር ሰራተኞች» ማለት በማዕከል፤ በፍርድ ቤቶች፤ በቅርንጫፍ፤ በሆስፒታል፤ በክሊኒክ፤ በክፍለ ከተማ፤ በወረዳ፤ በትምህርት ቤት እና በጤና ጣቢያ በወል ሰራ መደብ ላይ ተመድበው የሚሰሩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ማለት ነው።

2.12 «የቤት ኪራይ ድጎማ አበል» ማለት ለመንግስት ሰራተኞች ለቤት ኪራይ ክፍያ ድጎማ በየወሩ ከደመወዛቸው ጋር የሚከፈላቸው የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ ማለት ነው።

3. የፆታ አገላለጽ፤

በዚህ ሰነድ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

4. የሰነዱ አላማ፤

የዚህ ሰነድ አላማ የመንግስት ሰራተኞች የሚያነሱትን የኑሮ ውድነት ለማቃለል እንዲቻል የቤት ኪራይ አበል ድጎማ፣ መ.ያዊ የሥራ ሀላፊነት አበል፣የሞባይል ስልክና የትራንስፖርት አበል ጭማሪ በማድረግ የሰራተኛውን የስራ ተነሳሽነት እንዲጨምር እና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ለማድረግ ነው።

5. ሰነዱ የሚያካትታቸው ጥቅማ ጥቅሞች

ሀ/ የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል፤

ለ/ የመ.ያዊ የሥራ ሀላፊነት አበል

ሐ/ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል

መ/ የትራንስፖርት አበል

6. የስነዱ ወሰን፤

በዚህ አፈፃፀም ስነድ፤

ሀ/ የቤት ኪራይ ድጎማ አበል ክፍያ ቀደም ሲል የተፈቀደላቸዉ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ዲኖች እና አሰልጣኞች፣ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ ምህራን እና መምህራን፤ አቃቤ ህግ ባለሙያዎች፤ የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ዳኞች እና የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ዳኞችን አያካትትም።

ለ/ የሀላፊነት አበል ክፍያ ተፈፃሚ የሚሆነው በሆስፒታል እና ጤና ጣቢያ ላይ በሥራ ሀላፊነት ከቡድን መሪ ጀምሮ በተመደቡት እና በአማካሪ ላይ ነዉ።

ሐ/ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል ተፈፃሚ የሚሆነው በአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች፤ በሆስፒታል እና ጤና ጣቢያ ከቡድን መሪ ጀምሮ በተመደቡት እና በአማካሪ ላይ ነዉ ።

መ/ የትራንስፖርት አበል ተፈፃሚ የሚሆነው በአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች፤ በሆስፒታል እና ጤና ጣቢያ ከቡድን መሪ ጀምሮ በተመደቡት እና በአማካሪ ላይ ነዉ ።

ክፍል ሁለት
የጥቅማ ጥቅም አበል ክፍያ

7. የቤት ኪራይ ድጎማ አበል

በአሁኑ ሰዓት በከተማ አስተዳደሩ ካለው የቤት ችግር አንፃር የቤት ኪራይ በየጊዜው በመጨመሩ የመንግስት ሰራተኞች በከፍተኛ ደረጃ ተጎጂ በመሆናቸው በስራቸውና በማህበራዊ ህይወታቸው ላይ አሉታዊ ጫና የፈጠረባቸው ስለሆነ ለረጅም አመት ሰራተኞች በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያቀርቡበት የቆየውን ችግር በተወሰነ መልኩ ለማቃለል የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ለከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ሰራተኞች የቤት ኪራይ ክፍያ ድጎማ አበል በማጥናት ለውሳኔ አቅርቧል። በዚህም መሰረት፡-

ሀ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ዋና ፕሮቮስት፤ ምክትል ዋና ፕሮቮስት፤ አማካሪ፤ ለሆስፒታል ዋና ስራ አስኪጅ፤ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ እና ሜዲካል ዳይሬክተር የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል በወር ብር 6,000.00 /ስድስት ሺህ ብር/ እንዲከፈል፤

ለ/ ለጤና ጣቢያ ስራ አስኪያጅ፤ ምክትል ስራ አስኪያጅ እና ሜዲካል ዳይሬክተር የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል በወር ብር 3,000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ እንዲከፈል፤

ሐ/ በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል በወር ብር 4,500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፈል፤

በዚህ እንቀጽ በፊደል ሀ እና ለ ላይ ከተጠቀሱት ውጪ ያሉ የመንግስት ሰራተኞች

ሀ/ የወር ደመወዝ ከብር 1,100.00 እስከ ብር 3,999.00 ለሚከፈላቸው ሠራተኞች የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል በወር ብር 1,500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፈል፤

ለ/ የወር ደመወዝ ከብር 4,000.00 እስከ ብር 12,999.00 ለሚከፈላቸው ሠራተኞች የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል በወር ብር 1,250.00 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ አምሳ ብር/ እንዲከፈል፤

ሐ/ የወር ደመወዝ ከብር 12,999.00 በላይ ለሚከፈላቸው ሠራተኞች የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል በወር ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ የቤት ኪራይ ድጎማ አበል እንዲከፈል፤

8. ሙያዊ የሥራ ሀላፊነት አበል ክፍያ

ሀ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ዋና ፕሮቮስት የሀላፊነት አበል በወር ብር 2,000.00 /ሁለት ሺህ ብር/ እንዲከፈል፤

ለ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ምክትል ዋና ፕሮቮስት፣ አማካሪ፣ ለሆስፒታል ዋና ስራ አስኪጅ፣ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ እና ሜዲካል ዳይሬክተር የሀላፊነት አበል በወር ብር 1,800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር/ እንዲከፈል፤

ሐ/ ለጤና ጣቢያ ስራ አስኪያጅ፣ ምክትል ስራ አስኪያጅ እና ሜዲካል ዳይሬክተር የሀላፊነት አበል በወር ብር 1,500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፈል፤

መ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ እና ለሆስፒታል አላማ ፈጣሚ ዳይሬክተር/ ዲፓርትመንት ሃላፊ/ የሀላፊነት አበል በወር ብር 1,200.00 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር/ እንዲከፈል፤

ሠ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ እና ለሆስፒታል አላማ ፈጣሚ ቡድን መሪ የሀላፊነት አበል በወር ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ እንዲከፈል፤

ረ/ ለጤና ጣቢያ ዲፓርትመንት ሃላፊ/ የሀላፊነት አበል በወር ብር 700.00 /ሰባት መቶ ብር/ እንዲከፈል፤

ሰ/ ለጤና ጣቢያ ቡድን መሪ የሀላፊነት አበል በወር ብር 600.00 /ስድስት መቶ ብር/ እንዲከፈል፤

9. የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል

ሀ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ዋና ፕሮቮስት የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ እንዲከፈል፣

ለ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ምክትል ዋና ፕሮቮስት፣ አማካሪ፣ ለሆስፒታል ዋና ስራ አስኪያጅ፣ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ እና ሜዲካል ዳይሬክተር የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር ብር 800.00 /ስምንት መቶ ብር/ እንዲከፈል፣

ሐ/ ለጤና ጣቢያ ስራ አስኪያጅ፣ ምክትል ስራ አስኪያጅ እና ሜዲካል ዳይሬክተር የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር ብር 700.00 /ሰባት መቶ ብር/ እንዲከፈል፣

መ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ እና ለሆስፒታል አላማ ፈጣሚ ዳይሬክተር/ ዲፓርትመንት ሃላፊ/ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ እንዲከፈል፣

ሠ/ ለሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ እና ለሆስፒታል አላማ ፈጣሚ ቡድን መሪ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር ብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ እንዲከፈል፣

ረ/ ለጤና ጣቢያ አላማ ፈጣሚ ዲፓርትመንት ሃላፊ/ ቡድን መሪ/ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር ብር 350.00 /ሶስት መቶ ሀምሳ ብር/ እንዲከፈል፣

ሰ/ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች እና ተጠሪ ዳኛ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) እንዲከፈል፣

10. የትራንስፖርት አበል

ሀ/ ለሆስፒታል ፕሮቮስት፣ ምክትል ፕሮቮስት፣ ስራ አስኪያጅ፣ ምክትል ስራ አስኪያጅ፣ ሜዲካል ዳይሬክተር እና አማካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት መኪናና ነዳጅ በኖርመ. መሰረት፣

ለ/ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች እና ተጠሪ ዳኛ የትራንስፖርት አበል/የመዘዋወሪያ አበል በወር ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፈል፣

ሐ/ ለጤና ጣቢያ ስራ አስኪያጅ፣ ምክትል ስራ አስኪያጅ እና ሜዲካል ዳይሬክተር የትራንስፖርት አበል በወር ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ እንዲከፈል፣

መ/ ለሆስፒታል አላማ ፈጣሚ ዳይሬክተር/ ዲፓርትመንት ሃላፊ/ የትራንስፖርት አበል በወር ብር 700.00 /ሰባት መቶ ብር/ እንዲከፈል፣

ሠ/ ለሆስፒታል አላማ ፈዋሚ ቡድን መሪ የትራንስፖርት አበል በወር ብር 600.00 /ስድስት መቶ ብር/ እንዲከፈል፣

ረ/ ለጤና ጣቢያ አላማ ፈዋሚ ዲፓርትመንት ሃላፊ/ ቡድን መሪ/ የትራንስፖርት አበል በወር ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ እንዲከፈል፣

11. የውሎ አበል

11.1 ለፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ለመንገድ ጥርጊያ ሠራተኛ ብር 700.00 (ሰባት መቶ ብር)

11.2 ለጨበት መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ኤጀንሲ(በተደሞዉ አጠራር) ለጉድጓድ አዘጋጅ ብር 430.00 (አራት መቶ ሰላሳ ብር)

11.3 አዲስ ዙ ፓርክ ለፓርክ ፅዳት፣ ለእንስሳት መጋቢና ተንከባካቢ፣ ለሁለገብ ጥገና ሠራተኛ፣ ለጥበቃ ሠራተኛ ብር 400.00 (አራት መቶ ብር)

11.4 ለእሳትና አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን ተጠቃሚ ሠራተኞች ብር 400.00 (አራት መቶ ብር)

11.5 ለሌሎች ተቋማት ሠራተኞች ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር)

12. የደንድ ልብስ ማስፈያ

በእያንዳንዱ ተቋም የደንብ ልብስ ለሚያስፈልጋቸዉ ሠራተኞች የሚሰፈያ ዋጋ በአንድ በጀት ዓመት በጥቅሉ ብር 6,642.00 ሲሆን የተሻሻለዉ ብር 9,499.00

ክፍል ሶስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌ

1. ከአሁን በፊት የቤት ኪራይ ድጎማ ክፍያ አበል በተፈቀደላቸው ስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ማለትም የቱክኒክና መ/ያ ኮሌጅ ዲኖች እና አስልጣኞች፣ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ ምህራን እና መምህራን፣ አቃቤ ህግ ባለሙያዎች፣ የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ዳኞች እና የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ዳኞች በዚህ ስነድ አይከተቱም::

2. በዚህ ሰነድ የተፈቀደውን ጥቅማ ጥቅም በከተማ አስተዳደሩ በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ እውቅና የተቀጠሩ የኮንትራት ቅጥር ሰራተኞችም ተጠቃሚ ይሆናሉ።

3. በዚህ ሰነድ የተፈቀደው የቤት ኪራይ ድጎማ አበል ክፍያ ከስራ ግብር ነፃ ነው።

4. በእመት ፍቃድ፤ በወሊድ ፈቃድ፤ በሀዘን ፈቃድ፤ በህመም ፈቃድ በረዥም ጊዜ ትምህርት እና በአጭር ጊዜ ስልጠና ከመደበኛ ስራ ውጪ ሰሆነ ሰራተኛ የቤት ኪራይ ድጎማ አበል ክፍያ ይፈፀማል።

5. በዓመት ፈቃድ፤ በወሊድ ፈቃድ፤ በሀዘን ፈቃድ፤ በህመም ፈቃድ በረዥም ጊዜ ትምህርት እና በአጭር ጊዜ ስልጠና ከ30 ቀናት በላይ ከመደበኛ ስራ ውጪ ሰሆነ ሰራተኛ የሀላፊነት አበል፤ የስልክ ክፍያ አበል እና የትራንስፖርት አበል ክፍያ መፈፀም የተከለከለ ነው።

6. የተፈቀደው የጥቅማ ጥቅም አበል ክፍያ ከስራ ግብር ነፃ ነው።

7. የትራንስፖርት አበል የተፈቀደለት የሥራ ሀላፊ ወይም ሠራተኛ የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪ ከተመደበለት የትራንስፖርት አበል አይከፈለውም።

8. በዚህ ሰነድ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለቢሮው እየቀረበ እና ቢሮውም አጥንቶ ለካቢኔ በማቅረብ ውሣኔ የሚሰጥበት ይሆናል።

13. ተጠያቂነት

ይህን ሰነድ የተላለፈ ወይም የጣሰ ማንኛውም አመራር ወይም ፈጻሚ አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ህጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

14. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ ሰነድ ጋር የሚቃረን ማንኛውም በአስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት የወጡ ደንብ እና መመሪያዎች በዚህ ሰነድ በተጠቀሱት የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

15. ስነዱን ስለማሻሻል

ይህን ስነድ የከተማው አስተዳደር ፕብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ አዋንቱ በሚያቀርበዉ ካቢኔዉ ተወያይቶበት በከፊል ወይም መሉ በመሉ ሊያሻሽል ይችላል።

16. የስነዱ ዉሳኔ ሀሳብ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ስነድ በከተማው አስተዳደር ካቢኔ ከፀደቀበት ከ--------- ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

